| | |
|---|---|
| ግብጽ አረብ ሪፐብሊክ | ረቢዕ አወል 25/1441 ሂ. |
| አውቃፍ ሚኒስትር | ኑቨምበር 22/2019 ግ. |

# የህዝብን ጉዳይና አጠቃላይ ጥቅምን ማስከበር

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ
{وَتَعَاوَنُوا عَلَى الْبِرِّ وَالتَّقْوَىٰ وَلَا تَعَاوَنُوا عَلَى الْإِثْمِ وَالْعُدْوَانِ وَاتَّقُوا اللَّهَ إِنَّ اللَّهَ شَدِيدُ الْعِقَابِ}
ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም ( በበጎ ነገርና አላህን በመፍራትም ተረዳዱ፡፡ ግን በኃጢአትና ወሰንን በማለፍ አትረዳዱ፡፡ አላህንም ፍሩ፡፡ አላህ ቅጣተ ብርቱ ነውና፡፡) ማለት ነው፡፡
ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

እስልምና እውነተኛን አገር አዋቅሯል፡፡ መሰረቱን ያጠነከረና መዋቅሩንም ተመጣጣኝ ያደረገ ሲሆንም እሱን ለመጠበቅና ስለሱ ለመከላከል ሰዎች ጥረት እንዲያደርጉ ያሳስባል፡፡ የሀገረን አጠቃላይ ጥቅም ማስከበርና መጠበቅ ለዚህም ጉዳይ አስፈላጊውን ትኩረት መስጠት የመላው የሀገሪቱ ነዋሪዎች የጋራ ሃለፊነት መሆኑንም በግልጽ አስቀምጧል፡፡ ስለአጠቃላይ የህዝብ ጉዳዮችና እሴቶች አስፈላጊነት እንድሁም እነሱን ማጣጣል ስለሚያስከትለው ችግር አደገኛነት የማህበረሰቡ አባላት ግንዛቤ ባደገ ቁጥር እሱን ለመጠበቅ የሚኖረው ትብብር፣ አንድነትና ትስስር በዚያው ልክ ይጠናከራል፡፡ በዚህም የማህበረሰቡ መዋቅር ኃይል ጠንካራ ይሆናል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ያበሰረለትም የአንድ አካል ስሜት እውን ይሆናል፡፡
ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (አንድ ምእምን ለሌላው ምእምን ከፊሉ ድንጋይ ሌላውን እንደሚያጠናክር የአንድ ግንብ አካል ነው፡፡ ጣቶቻቸውን

በማጠላለፍም ሁኔታውን አስረድተዋል፡፡) እንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ብለዋል፡ (ምእምናን በመዋደዳቸው፣ በመተዛዘናቸውና በመተጋገዛቸው ከሱ የአንዱ አካል ክፍል ባሰሞተ ጊዜ የሌላው አካል ከፍሎች እንቅልፍ በማጣትና በህመም እንደሚጠራራ አንድ አካል ናቸው፡፡)
የሰውን ልጅ መንፈስ ከለኔ ብቻ ባይነት ተንኮል ለማዳን ሲባል ፋይዳው ለመላው የማህበረሰቡ አባላት የሆነውን የሰፊውን ህዝብ ጥቅም ፋይዳው ለግለሰቦች ብቻ ከሆነው ጠባቡ ጥቅም ማስቀደም ከአጠቃላይ ጉዳይ ጥበቃ መዋቅሮች ዋነኛው መሆኑ ጥርጥር የለበትም፡፡ ይህውም አጠቃላይ ጥቅም ለመላ ማህበረሰቡ ቁሳዊም በሆኑም ይሁን ቁሳዊ ባልሆኑ ነገሮች ለሰዎች ደግን ሁሉ የሚያሚያመጣ፣ በአንፃሩም መጥፎ ነገሮችንና ብልሹነትን የሚከላከል በመሆኑ ነው፡፡ ከዚያም አልፎ ለሀገር ደህንነትና መረጋጋት እንድሁም ለሀገር አንድነት እጅጉን አስፈላጊ ነው፡፡ የህዝብ አጠቃላይ ጥቅም መከበር የሃይማኖት ህግ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ነገሮች አንደኛው ነው፡፡
የተከበረው ቁርአን የመላ ማህበረሰቡን ጥቅም ማስከበርና እሱንም ከግለሰብ ጥቅም ማስቀደም የመላ ነያብት ስርኣት መሆኑን አረጋግጧል፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) አንድንም ነብይ ወይም መልክተኛን አላከም ቁሳዊ ምንዳንና ዓለማዊ ጥቅምን ያለመፈለግ የህዝቡን ደስታ እውን ለማድረግ ቢሆን እንጂ፡፡ ታላቁ አላህ በነብዩ ኑሕ (ዐ.ሰ.) ልሳን እንድህ ይላል፡

وَيَا قَوْمِ لا أَسْأَلُكُمْ عَلَيْهِ مَالًا إِنْ أَجْرِيَ إِلَّا عَلَى اللَّهِوَمَا أَنَا بِطَارِدِ الَّذِينَ آمَنُوا إِنَّهُمْ مُلَاقُو رَبِّهِمْ وَلَكِنِّي أَرَاكُمْ قَوْمًا تَجْهَلُونَ}

ትርጉሙም («ሕዝቦቼም ሆይ! በርሱ (በተላክሁበት ማድረስ) ላይ ገንዘብን አልጠይቃችሁም፡፡ ምንዳዬ በአላህ ላይ እንጂ በሌላ ላይ አይደለም፡፡ እኔም እነዚያን ያመኑትን አባራሪ አይደለሁም፡፡ እነርሱ ጌታቸውን የሚገናኙ ናቸውና፡፡ ግን እኔም የምትሳሳቱ ሕዝቦች ሆናችሁ አያችኋለሁ፡፡») ማለት ነው፡፡ እንድሁም በሁድ (ዐ.ሰ.) ልሳን እንድህ ይላል፡

يَا قَوْمِ لَا أَسْأَلُكُمْ عَلَيْهِ أَجْرًا إِنْ أَجْرِيَ إِلَّا عَلَى الَّذِي فَطَرَنِي أَفَلَا تَعْقِلُونَ}

ትርጉሙም («ሕዝቦቼ ሆይ! በእርሱ (በማድረሴ) ላይ ምንዳን አልጠይቃችሁም፡፡ ምንዳዬ በዚህ በፈጠረኝ ላይ እንጂ በሌላ ላይ አይደለም፡፡ አታውቁምን) ማለት ነው፡፡በሹዓይብ ልሳን ደግሞ እንድህ ይላል፡

{إِنْ أُرِيدُ إِلَّا الْإِصْلَاحَ مَا اسْتَطَعْتُ وَمَا تَوْفِيقِي إِلَّا بِاللَّهِ عَلَيْهِ تَوَكَّلْتُ وَإِلَيْهِ أُنِيبُ} .

ትርጉሙም (በተቻለኝ ያክል ማበጀትን እንጂ አልሻም (ለደግ ሥራ) መገጠሜም በአላህ እንጂ በሌላ አይደለም፡፡ በእርሱ ላይ ተመካሁ፡፡ ወደእርሱም እመለሳለሁ፤» አላቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

የቅኑ ሃይማኖት ህግጋቶች ለሰው ልጅ አእምሮ ተስማሚ ሆነው ነው የተቀመጡት፡፡ በመሆኑም ለመላ የሀገር ነዋሪዎች ጥቅም የሚያስከብርን ነገር ሁሉ እውን እንድናደርገው አዞናል፡፡ እንድሁም እንደያስፈላጊነቱ እጅግ አስፈላጊውን እንዲናስቀድምም አስገንዝቦናል፡፡ ለምሳሌ ድሆችን ለማከምና ለመንከባከብ ጤና ጣቢያ ማዋቀርና በአስፈላጊ መገልገያዎች ማነጹ የወቅቱ አንገብጋቢ ጉዳይ ከሆነ ለሱ ቅድሚያ መስጠት ግዴታ ይሆናል፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ ትምህርት ቤቶችንና የትምህርት ተቋማትን መዋቀር መገልገያዎችን ማሟላት እንድሁም ለተማሪዎች የሚያስፈልጋቸውን ነገር ማቅረብ በጣም ተፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ለዚህ ጉዳይ ቅድሚያ መስጠት ይኖርብናል፡፡ አሁንም እዳ ያለባቸውን ሰዎች እዳ መክፈል፣ የችግረኞችን ጭንቀት ማቃለል አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ለሱ ቅድሚያ ይሰጠዋል፡ የሰዎችን ጉዳይ ማውጣት የህግና የሀገራዊ ግዴታ ነው፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (ካጠገቡ ጎረቤቱ መራቡን እያወቀ እስኪጠግብ በልቶ ያደረ ሰው በኔ አላመነም፡፡)

ከአጠቃላይ ጉዳዮች ጥበቃ ሌላው ደግሞ መላ ነዋሪዎች የሚጋሩበት የህዝብን ገንዘብ መጠበቅ የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ በውስጡ የተካተቱት መብቶች ብዛት ያላቸው በመሆኑና የባለመብቶቹ ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑ የህዝብ ገንዘብ እርምነት ከግል ገንዘብ እርምነት በጣም ይጠብቃል፡፡ በመሆኑም የአስልምና እምነት የህዝብን ገንዘብ ከማጥፋት፣ ከመስረቅና በሱም ላይ ጉዳት ከማድረስ እንድንታቀብ በጥብቅ አስጠንቅቆናል፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَمَنْ يَغْلُلْ يَأْتِ بِمَا غَلَّ يَوْمَ الْقِيَامَةِ ثُمَّ تُوَفَّى كُلُّ نَفْسٍ مَا كَسَبَتْ وَهُمْ لاَ يُظْلَمُونَ}

ትርጉሙም (ሰለባንም የሚደብቅ ሰው በትንሣኤ ቀን በደበቀው ነገር (ተሸክሞ) ይመጣል፡፡ ከዚያም ነፍስ ሁሉ የሥራዋን ዋጋ ትሞላለች፡፡ እነርሱም አይበደሉም፡፡) ማለት ነው፡፡

የህዝብ ገንዘብ የመላ ነዋሪዎች ንብረት እንጂ የግለሰብ ወይም የተለየ ቡድን ገንዘብ አይደለም፡፡ በመንግስት ገንዘብ ዙሪያ የሚሰሩ ሰዎች አደራ ጠባቂዎች

በመሆናቸው ከሱ በጭቀው መውሰድ ወይም በሱ ጉዳት ማድረስ በደልና ክዳት መፈጸም እንድሁም የሰዎችን ገንዘብ በከንቱ መብላት ይሆንባቸዋል፡፡ የእስልምና እምነት አጠቃላይ የህዝብ መገልገያዎችንም እንድነጠብቅ አዞናል፡፡ የአምልኮ ማድረሻ ቤቸት፣ ትምህርት ቤቶች፣ ሆስፒታሎች፣ የህዝብ መዝናኛዎችና ሌሎችም አጠቃላይ የህዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የህዝብ ንብረቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም በነሱ ላይ ጉዳት ማድረስን፣ ማውደምንና በማንኛውም መልኩ ማበላሸትን የእስልምና እምነት በጥብቅ ከልክሏል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَلَا تُفْسِدُوا فِى الْأَرْضِ بَعْدَ إِصْلَاحِهَا}

ትርጉሙም (በምድርም ውስጥ ከተበጀች በኋላ አታበላሹ፡፡) ማለት ነው፡፡
አንዳንድ ሰዎች በህዝብ ንብረት የጋራ መብት አለን በማለት በፈለጉት መልኩም መጠቀም እንደሚችሉ በከንቱ በማሰብ ከመሳሳት ሊጠነቀቁ ይገባል፡፡ የህዝብ መገልገያ ተቋማት በአንድ ዘመን የሚኖር ግለሰብ ወይም ቡድን ንብረት ሳይሆኑ በአሁኑ ዘመን የሚኖሩ የሁሉም ህዝብና የመጭውም ትውልድ ንብረት በመሆናቸው ልንጠበቃቸው፣ ልንከባከባቸውና ልናበለጽጋቸው ይገባል፡፡
ከአጠቀላይ መገልገያዎች ሌላው ደግም መጓዣ መንገድ ነው፡፡ መንገድን መጠበቅና የሱንም መብት ማስከበር የሁሉም ሰው ግዴታ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (አደራ በመንገዶች ላይ እንዳትቀመጡ፡፡) ባለደረቦችም የአላህ መልክተኛ ሆይ በመንገዶች ተቀምጠን መጨዋወታችን አይቀሬ ነው አሉ፡፡ ያን ጊዜ የአላህ መልክተኛ (ከመቀመጥ መታቀብን አሻፈረኝ ካላችሁ ደግሞ የመንገድን መብት ማስከበር ይኖርባችኋል) አሉ፡፡ እነሱም የመንገድ መብቱ ምንድን ነው? በማለት ጠየቁ፡፡ እሳቸውም (ዓይንን ማየት ከማይፈቀድላት ነገር መከልከል፣ ጉዳት ከማድረስ መታቀብ፣ ለሰላምታ መልስ መስጠት፣ በመልካም ምግባር ማዘዝና ከመጥፎ ነገርም መከልከልነው) አሉ፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በሌላ ሐዲስ እንድህ ብለዋል፡ (እምነት ሰባ ከምናምን ወይም ስድሳ ከምናምን ከፍሎች አሉት፡፡ እጅግ በላጩ፡

لاَ إِلَهَ إِلاَّ اللهُ

« ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ የለም» ማለት ሲሆን ዝቅተኛው ደግሞ ጎጂነ ገርን ከመንገድ ማስወገድ ነው፡፡ የአክብሮት ሀፍረትም የእምነት አካል ነው፡፡)

ከአጠቃላይ ጉዳዮች ሌላው ደግሞ የብሄራዊ አገልግሎት ግዴታን መወጣት ነው፡፡ የብሄራዊ አገልግሎት ግዴታን መወጣት አንድ ሰው ለሃይማኖቱና ለሀገሩ ከሚወጣቸው ግዴታዎች በጣም ታላቁ ሲሆን ለሀገሩ ያለውን ፍቅርና ታማንነት የሚገልጽበት ግዴታም ነው፡፡ ሀገርና ክብር ለአንድ ሰው ከሕይወቱ፣ ከሃይማኖቱና ከንብረቱ ያነሰ ግምት ሊሰጣቸው አይገባም፡፡ የብሄራዊ ግዴታ በአንድ ሰው ጀግንነት፣ ወኔና መልካም እሴት በማስረጽ ታላቅ ሚና አለው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ሁለት ዓይኖች እሳት አይነካቸውም፡፡ እነሱም አላህን በመፍራት ያለቀሰች ዓይንና በአላህ መንድ ዘብ ያደረች ዓይን ናቸው፡፡)

መከበር ካለባቸው አጠቃላይ ጥቅሞች ሌላው ደግሞ ከመንግስትና ከሌላ አገር ወይም ከመንግሰትና ከውጭ ድርጂቶች መካከል ያሉ ጉዳዮችን ማክበር ነው፡፡ ማንኛውም ህጋዊ፣ ሀሳባዊ ወይም ሰበካዊ ሂደት ከሀገረ ገዢው ወይም ከወኪሉ የተላለፈ ውሳኔ ያለው ድርጂታዊ ገጽታ የያዘ ሂደት መሆን አለበት፡ በዚህ ጉዳይ ላይ መግለጫ የሚሰጥ ሰው ሁሉ ከወቅታዊ ተባጩ ሁኔታ ወይም ደግሞ ከአላም አቀፍ ህግ፣ ቃል ኪዳንና ስምምነቶች ጋር የሚጋጭ መልእክት እንዳያስተላለፍ ማሀበራዊ ሀገራዊና አለም አቀፋዊ ደንቦችን መጠበቅ ይኖርበታል፡፡ አላህ (ሶ.ወ.) ቃልን እንድናከብር እንድህ በማለት አዞናል፡

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ ءَامَنُوا أَوْفُوا بِالْعُقُودِ}

ትርጉሙም(እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በቃል ኪዳኖች ሙሉ፡፡) ማለት ነው፡፡ ይህች አንቀጽ አንድ ሰዎ ከሌላው ሰው ጋር የሚያደርጋቸውን ሁሉንም ውሎች፣ ቃል ኪዳኖችና ስምምነቶችን የሚያካትት አጠቃላይ ደንብ ያቀፈች መሆኑን ሊቃውንት ይጠቁማሉ፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ ( ሙስሊሞች እርም የሆነን ነገር የተፈቀደ ወይም የተፈቀደውን ነገር እርም ያደረገ እስካልሆነ ድረስ ያስቀመጡትን መስፈርት አክባሪዎች ናቸው፡፡)

እነሆ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከቁረይሾች ጋር የገቡተን የሑደይቢያን ቃል ኪዳን በማክበር ችገር ሊደርስባቸው የሚችል መሆኑ ቢገመተም (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ በሲርን ወደ ቁረይሾች መለሰዋል፡፡ ይህ ተግባር በአንድ በኩል ቃል ኪዳንን ማክበር ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የማሀበረሰቡን ጥቅም ከገለሰቡ ጥቅም ማስቀደም ነው፡፡

አንድ ሰው ያለ ሙሉ ግንዛቤ በአጠቃላይ ጉዳይ መግለጫ በመስጠት የሀገረን መዋቅር ሊያዛባ ይችላል፡፡ ምክኒያቱም በዚህ ተግባሩ የሀገርን

ደህንነት እንደራሱ የግል ግጦሽ መስክና እንደመዝናኛ ቁስ በማድርግ በሚያውቀውም በማያውቀውም ሲያወራ ጥቅም በማምጣት ፋንታ ምድር ላይ ብልሹነትን ያስፋፋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ነገሮችን ወደአዋቂዎች እንድንመልስ እንድህ በማለት አዞናል፡

**{وَإِذَا جَاءَهُمْ أَمْرٌ مِّنَ الْأَمْنِ أَوِ الْخَوْفِ أَذَاعُوا بِهِ وَلَوْ رَدُّوهُ إِلَى الرَّسُولِ وَإِلَى أُولِي الْأَمْرِ مِنْهُمْ لَعَلِمَهُ الَّذِينَ يَسْتَنبِطُونَهُ مِنْهُمْ وَلَوْلَا فَضْلُ اللَّهِ عَلَيْكُمْ وَرَحْمَتُهُ لَاتَّبَعْتُمُ الشَّيْطَانَ إِلَّا قَلِيلًا} .**

ትርጉሙም (ከጸጥታ ወይም ከፍርሃት አንዳች (ወሬ) በመጣላቸውም ጊዜ እርሱን ያጋንናሉ፡፡ ወደ መልክተኛውና ከእነርሱ ወደ ትዕዛዙ ባለቤቶች (ወደ ዐዋቂዎቹ) በመለሱት ኖሮ እነዚያ ከእነርሱ (ነገሩን) የሚያውጣጡት ባወቁት ነበር፡፡ በእናንተም ላይ የአላህ ችሮታና እዝነቱ ባልነበረ ኖሮ ከጥቂቶች በስተቀር ሰይጣንን በተከተላችሁ ነበር፡፡) ማለት ነው፡፡

ይህ ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንትም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁኝ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች ሆይ!**

የአጠቃላይ ጉዳይ ግንዛቤ ከተወሰነው የግል አስተሳሰብ በላይ በአለው በማህበረሰቡ አስተሳሰብ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህም አንፃር ይህ ጉዳይ ለግለሰቦች የተፈቀደ ወሰን የለሽ ጉዳይ ሳይሆን የተጣለባቸውን ኃላፊነት እሴት ጠንቅቀው የሚያውቁ የግል ባለሞያዎች ድርሻ ነው፡፡ እነዚህ ወገኖች የብሄራዊ ደህንነት፣ የሰዎች ህይወት፣ የህዝብ ጥቅም፣ የእምቅ ሀገር ሀብት፣ የሀገርን ክልላዊና አለም አቀፋዊ ቦታ በማስከበር፣ የፖሊቲካ፣ የማህበራዊ፣

የሳይንሳዊና የሌሎችንም የህዝብ መገልገያ ነገሮችን አስመልክቶ የተሰጣቸውን ሃላፊነት በሚገባ የመወጣት ብቃት አላቸው፡፡
የእውቀት ባለቤቶች አንድ የምርምር ጥናት የማድረግ ብቃት ያለው ሰው የተለየ ሞያ ባካበተበት ዘርፍ ለህዝብ ጥቅም የምርምር ጥናት አድጎ በሰጠው ብያኔ ቢሳሳት አንድ መንዳ(የጥናቱ ጥረት) ካልተሳሳተ ደግሞ ሁለት ምንዳ ያለው መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ የዚህ እሳቦት ተቃራኒ ግንዛቤም አንድ ሰው እውቀት ሳይኖረው በዘርፉ የተለየ ሞያ ሳያካብት የምርምር ጥናት አድርጎ ብያኔ በሚሰጥበት ወቅት ባይሳሳትም ያለእውቀት በመዳፈሩ አንድ ወንጀል ቢሳሳት ደመግሞ የማዳፈሩና የስህተቱ ሁለት ወንጀል እንደፈጸመ ይሆናል ማለት ነው፡፡ የእስልምነ እምነት ለባለእውቀቶችና ለባለልዩ ሞያወች ልዩ ክብር ሰጥቷል፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{فَاسْأَلُوا أَهْلَ الذِّكْرِ إِن كُنتُمْ لَا تَعْلَمُونَ}**
ትርጉሙም (የማታውቁም ብትኾኑ የዕውቀትን ባለቤቶች ጠይቁ፡፡) ማለት ነው፡፡
የእውቀት ባለቤት ማለት የእውቀትና የልዩ ሞያ ባለቤቶች ማለት ነው፡፡ ከዚህም አንፃር ያለ እውቀትና ያለመረጃ በመቻኮል የሚሰጥ የሃይማኖት ብያኔ ተከልክሏል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡
**{فَمَنْ أَظْلَمُ مِمَّنِ افْتَرَى عَلَى اللَّهِ كَذِبًا لِيُضِلَّ النَّاسَ بِغَيْرِ عِلْمٍ إِنَّ اللَّهَ لَا يَهْدِي الْقَوْمَ الظَّالِمِينَ}**
ትርጉሙም ( ሰዎችንም ያለ ዕውቀት ሊያጠም በአላህ ላይ ውሸትንም ከቀጠፈ ሰው ይበልጥ በደለኛ ማን ነው አላህ በደለኞችን ሕዝቦች (ቅኑን መንገድ) አይመራም፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡
**{وَلَا تَقُولُوا لِمَا تَصِفُ أَلْسِنَتُكُمُ الْكَذِبَ هَذَا حَلَالٌ وَهَذَا حَرَامٌ لِّتَفْتَرُوا عَلَى اللَّهِ الْكَذِبَ إِنَّ الَّذِينَ يَفْتَرُونَ عَلَى اللَّهِ الْكَذِبَ لَا يُفْلِحُونَ * مَتَاعٌ قَلِيلٌ وَلَهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ}**
ትርጉሙም (በአላህም ላይ ውሸትን ልትቀጣጥፉ ምላሶቻችሁ በሚመጥኑት ውሸት «ይህ የተፈቀደ ነው፤ ይህም እርም ነው» አትበሉ፡፡ እነዚያ በአላህ ላይ ውሸትን የሚቀጣጥፉ አይድኑም፡፡ ጥቂት መጣቀም አላቸው፡፡ ለእነሱም አሳማሚ ቅጣት አላቸው፡፡) ማለት ነው፡፡
ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (ያለእውቀት ብያኔ የሰጠ ሰው የዚያ ብያኔ የሰጠበት ነገር ኃጢያት አለበት፡፡) (ከነርሱ አላህ ይውደድና) ተላላቅ የነብያችን ባልደረቦች በምንም ነገር ብያኔ ከመስጠት ይሳቀቁ ነበር፡፡

ይህውም ሊያስከትለው የሚችለውን አደጋ ስለተገነዘቡ ነው፡፡ እነሆ ሰይዲና አቡ በክር አሲዲቅ ‹ከአለህ (ዐ.ወ.) መጽሐፍ የማላውውን ነገር ከተናገርኩኝ የተኛው ሰማይ ይጠልለኛል የትኛዋስ መድር ትሸከመኛለች፡›) ይሉ ነበር፡፡ ሻዕቢይ የተባሉት ሊቅ ስለአንድ ነገር ተጠየቁና አላውቅም አሉ፡፡ ያንጊዜ ባልደረቦቻቸው እኛ ስለርሶ አፈርን አሏቸው፡፡ እሳቸውም ነገር ግን የአላህ መላእክት (ያሰወቅህንን እንጂ ሌላን ነገር አናውቅም) ባሉ ጊዜ አላፈሩም በማለት መለሱ፡፡

የአጠቃላይ ጉዳይ ጥበቃ ሁሉም በአለበት ቦታና በችሎታው መጠን የያንዳንዱ ባለሞያ ሃላፊነት ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (ሁላችሁም ጠባቂዎች ናችሁ፡፡ ሁላችሁም ስለምትጠብቁት ነገር ትጠየቃላችሁ፡፡ አንድ መሪ ጠባቂ ነው፡፡ ስለሚጠብቀውም ነገር ይጠየቃል፡ ፡ አንድ ሰው የቤተሰቡ ጠባቂ ነው፡፡ ስለሚጠብቀውም ነገር ይጠየቃል፡፡ አንድ ሴትም የባሏ ቤት ጠባቂ ናት፡፡ ስልምትጠብቀውም ነገር ትጠየቃለች፡ ፡ አንድ አገልጋይ የጌታው ገንዘብ ጠባቂ ነው፡፡ ስለሚጠብቀውም ነገር ይጠየቃል፡፡)

በርካታ ሰዎች የሚናገሩትን፣ የሚጽፉትን ወይም በማህበራዊ ደረ ገጽ የሚሳተፉበተን ነገር እንደቀላል ነገር ይመከቱታል፡፡ ይልቁንም ከፈሎቻችን እንደመዝናኛ እንመለከተዋልን፡፡ ይህውም ከሰዎች መካከል አሉባልታን መፍጠርና ማናፈስ የከንቱ ሰዎች ከእውነት ሰዎች ጋር በሚያደርጉት ትግል የሚጠቀሙበት የማፍረሻ አደገኛ መሳሪያ መሆኑን በመዘንጋት ነው፡፡ ውጤቱም የአንድ አካል ህዝቦች አንዱ ሌላውን በጥርጣሬ ዓይን መመልከት እንድሁም አንዱ ሌላውን ማስፈራራት ይሆናል፡፡ ለዚህም ነው ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) (አንድ ሰው ለመዋሸቱ መረጃነት የሰማውን ሁሉ ማውራቱ በቂ ነው) ያሉት፡፡

አንድ ሰው የሰማውን ሁሉ ማውራቱ የሚቀጣበት የውሸት መረጃ ከሆነ ያላየውን ያልሰማውንና የማያውቀውን ፈጥሮና ቀጥፎ የሚያወራ ሰው ቅጣት ምን ያህል ከባድ እንደሚሆን መገመት አያዳግትም፡፡ አድማስ የሚሻገሩና በትንሳኤ ቀን ለባለቤታቸው ስቃይ ምክኒያት የሚሆኑ ቀላት እጅግ በርካቶች ናቸው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አንድህ ይላሉ፡ (አንድ የአላህ ባሪያ ግምት የማይሰጠው መልካም ቃል ይናገርና አላህ ዘንድ ተወዳጅ ሆኖ አላህ በሱ ከፍተኛ ደረጃዎችን ሊሰጠው ይችላል፡፡ እንድሁም አንድ የአላህ ባሪያ ግምት የማይሰጠው መጥፎ ቃል ይናገርና አላህን አስቆጥቶ አላህ በሱ ጀሀነም ሊዘፍቀው ይችላል፡፡) ከዚህም አንጻር ልብ ማለትና ጥንቃቄ ማድረግና

ስለማናውቀው ነገር ከመናገርና ያለእውቀት ብያኔ ከመስጠትም መታቀብ ይኖርብናል፡፡
አላህ (ሱ.ወ.) ስለማንኛውም የምንሰማው ወሬ ቀድመን እንድናረጋግጥና እንዲናጣራ አንድህ በማለት አዞናል፡

يَاأَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا إِنْ جَاءَكُمْ فَاسِقٌ بِنَبَإٍ فَتَبَيَّنُوا أَنْ تُصِيبُوا قَوْمًا بِجَهَالَةٍ فَتُصْبِحُوا عَلَى مَا فَعَلْتُمْ نَادِمِينَ}

ትርጉሙም (እላንተ ያመናችሁ ሆይ! ነገረኛ ወሬን ቢያመጣላችሁ በስህተት ላይ ኾናችሁ ሕዝቦችን እንዳትጎዱና በሥራችሁት ነገር ላይ ተጸጸኞች እንዳትኾኑ አረጋግጡ፡፡) ማለት ነው፡፡
ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አንድህ ብለዋል፡ (እርጋታ ከአላህ ነው፡፡ መቻኮል ደግሞ ከሰይጣን ነው፡፡)
እኛ በአሁኑ ወቅት ስለአጠቃላይ ጉዳይ ጥልቅ ግንዛቤ ሊኖርን ይገባል፡፡ የአጠቃላይ ጥቅምን ማስቀደም፣ ስለሚሸመንልን አደጋ ማወቅ ለኛ አጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ በሌሎች መገሰጽ ሲኖርብን ጠላች እንደሌሎች አዳልጦን እንዲንወድቅ ለሚያደርጉት ጥረት አድል ላለመስጠት አንድነታችን ማጠናከር አንድሁም ጥቅሙ መላ የሰው ልጅን የሚሸፍን በሆነ በመልካም ሥራ መተጋገዝና መተባበር ያስፈልገናል፡፡

ጌታችን ሆይ የሀገራዊ ግዴታችንን እንድንወጣ ረደኤትህ ከኛ ጋር ይሁን፡፡ ህዝባችንን መሪዎቻችንን አንድሁም ሀገራችንን ጠብቅልን፡፡ አሜን፡፡